"እስኪነጋ ድረስ" (አዲስ አበባ 1996 ዓ.ም.) ከተባለው የታሪኳ ገብረየስ የግጥም መድበል የተወሰዱ ግጥሞች

## ጭብጨባ

አይከፋም ጥሩ ነው ፣
አንስቶ የሚጥለው ፣
ያው መጠሪያ ስሙ እርሱ ጭብጨባ ነው ::
እናማ ጥሩ ለሰራ ሰው ፣
አዎን ይገባዋል ፣
ለልፋቱ ውጤት ጭብጨባ ያሻዋል ::
ግን! ምንም ላልሰራ ሰው ሲጨበጨብለት ፣
እድገት አይሆነውም ለእርሱ እንዘንለት ::
ገና ነህ እንበለው አናጨብጭብለት
ጭብጨባ ፣
ለፍቶ ለጣራ ሰው
ነውና የሚገባ ::

## ሕይወት

ሽቅብ ፣
ቁልቁል ፣
ውጣ ውረድ የበዛባት ፣
ደስታ ሀዘኑ ፣
የሚፈራረቅባት ::
አንደኛው ሲያለቅስ ፣
ሌላው የሚስቅባት ፣
አንዱ ጋ ሲሰረግ ፣
ሌላ የሚሞትባት ፣
ዛሬ ላይ ተቀምጦ ፣
ነገ አይታይባት ፣
ገና ላልጀመራት ፣
ሕይወት አስፈሪ ናት ::

## ሆኖ መገኘት ነው

ጫማህን ተጫምተህ ፣
ሱሪህን አጥልቀህ ፣
ኮትህን ደርበህ ፣
መዞርህን ተወው ፣
ራስህን አታታል ፣
ጊዜው በጣም ከፍቷል ::
ከተያዙ መዳን ፣
ድሮ ነበር ቀርቷል ::
ራስህን እወቅ ፣
የኋላ የኋላ ፣
አላዋቂ እንዳታልቅ ::
በኋላ ስትያዝ እንባህን መርጨቱ ፤
እርሱ አይረባህም ፣
ስለሆነ ከንቱ ::
አሁን የሚረዳህ ፣
ለብሶ መሄድ ሳይሆን ሆኖ መገኘት ነው ::
ራስህን ካዳንክ ፣
ዘንድሮ ድልህ ነው ::
ቆሞ መሄድ ከንቱ ፣
ሆኖ መገኘት ነው ::

## ርቃ ስትሄድ

ሳይጨልም ቀናቱ ስትሄድ ተሻግራ ፣
የጨለማን ኑሮ ለእኔ ብላ መርጣ ፣
ጥበብን ተጠምታ በደንብ ልትጠግበው ፣
ወደአፈር ስትገባ ዓለም በቃኝ ብላው ፣
የፊርማን መቀደድ ማነው ያስተዋለው ፣

ከሀቅ አብራክ ወጥታ ለሀቅ ብላ ሞተች ፣
ዳግም ላትመለስ አምራ ተጓዘች ፡፡
አትዘኑ ሰዎች አታንቡ በጣሙን ፣
የፊርማ ሥራዎች ይላሉ አንብቡን ፡፡
ዝም አትበይ ተናገሪ ፣
ሆድ ያባውን እስኪ አውሪ ፡፡
አረ ሀናም ብቻዋን ነች ፣
ያንቺ ግጥምስ ምንድን አለች ፡፡
«ምን ዞሮብኝ ይሆን ምንድን አቀመስሽኝ ፣
እየሞትኩ ላኖርሽ እንድመኝ ያረግሽኝ»
ብለሽ አንብቢልኝ ማራኪ ግጥምሽን ፣
እንኪ ብለሽ ስጭኝ የያኔው ተስፋሽን ፡፡
እንግዲህ ፊርማዬ በአይኔ እያየሁሽ ካፈሩ ከገባሽ ፣
ሌላ ምን እላለሁ ጌታ እግዚአብሔር ይርዳሽ ፣

*የዚህች ግጥም መታሰቢያነት*
*በሞት ለተለየችን ለገጣሚ ፊርማዬ አለሙ*

## እስኪነጋ ድረስ

ለአንተ እየነጋልህ ፣
ለእኔ እየጨለመ ፣
አንተን ካፈቀርኩህ ፣
ጊዜው ከራረመ ፡፡
ግና የኔ ጌታ ፣
የጨለማው ሌሊት ፣
መንጋቱ አይቀርም ፣
ለመንጋት መጨለም ፣
ግዴታ ቢሆንም ፡፡

---

**The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot. **You may contact Tarikua Gebreyes for comments at** ***tarikua_11@yahoo.com***